# “አባ” ሆይ! በሥምዎ ሐወልትስ ሰርተዋል የቀሮት መርከብ ነው ወደብ ግን የሎትም!!

- “አባ” ሆይ! በምስልዎና በሥምዎ ያቆሙት ሐውልት ይቅር ለነፍስ ለሥጋዎትም አይጠቅምም ብዬ ስጽፍሎት በአክብሮት ነው!!
- “አባ” ሆይ! ይህን ሐወልት በሥምዎ ከማስቀረጽዎ ይልቅ ቂርቆስና ተክለሃይማኖት የወደቁትን ነዳያኖችችን ማየት ለተሳኖት ዓይንዎ መንፈሳዊ መነጽር ቢገዙበት ይበጅዎት ነበር ነው የምለው ድንጋይ በድንጋይ ላይ ለመቆለል ከመሮጥ ይልቅ።
- “አባ” ሆይ! ዙሪያውንን የከበቦት ምእመን የደም ዕንባ እያለቀሰቦት ከምንም ሳይቆጥሩት ሐወልት በስምዎና በምስሎዎ ማስቀረጽዎ ለኢትዮጵያ ህዝብ ያሎትን ጥላቻና ንቀት መግለጽዎ አይደል!
- “አባ” ሆይ! የቀን እጁ የሆነው ወያኔ ትናንትና የሌኒን ኢንጅልስና የማርክስን ሐወልት በክሬይን አንገታቸውን እንደ ደሮ አንቆ ከመዲናችን ከአዲስ አበባ ዕንብርት ነቃቅሎ በአፍ ጢማቸው እንደደፋ ሁሉ ያለቀሶቦት ምእመን የእርስዎን ሐወልት ደግሞ እንደሚፈጠፍጠው በህይወት ዘመንዎ ያዩታል ነው የምሎት!
- “አባ” ሆይ! ታሪክ እንደሚመሰክረው ትናንትና ለኃይማኖታቸው ሲሉ ለእግራችን እንኳ ጫማ አናጠልቅም በማለት በዱር በገደል ሲንከራተቱ ህይወታቸው ባለፈችው በእነ አቡነ ተክለሃይማኖት እግር ዘመነኛውን (ቄንጠኛ) “አባታችን” ላሳየን መድኃኒአለም ክብርና ምሥጋና ይግባው!!
- “አባ” ሆይ! የንቀትዎ ንቀት ሐወልት በስሜ ላሳንጽ ነው ብለው ቀድሞ ያልነገሩትን ምእመን በመረቃው ዕለት ሪፖርትን አስነበቡበት ስሰማ ይህን ያደረጉበት ምክንያትዎ አልገባኝምና ምክንያትዎ ምን ይሆን? አሁንም በድጋሜ ይሄ “ጭቃ!” ሕዝብ ምን ያመጣል ማለትዎ ይሆን?
- “አባ” ሆይ! ድመት ወተት ስተሰርቅ ዓይንዋን ጨፍና ነው በስዋ ቤት (አዕምሮ) የእኔ ዓይን እደተጨፈነ የሚያየኝም ሰው ዓይን ይጨፈናል ብላ ስለ ምትገምት ነው። “አባ” ሆይ! ይህን ሁሉ ግፍና በደል የሚፈጹሙበት ምእመን የለም አያይም! በማለት ይሆን?
- ታላቁ ንጉሥ ዳዊት የእግዚአብሔር ባርያ እኔ ባማረ ቤት ተቀምጬ የአምላኬ የእግዚአብሔር ታቦት በየድንኳኑ ይንከራተታል በማለት ለአምላኬ ታቦት ቤት እስራለታልሁ ብሎ ለመቅደሱ መስሪያ ዕቃዎችን ሁሉ ካዘጋጀ በኋላ ልዑል እግዚአብሔር አንተ አትሰራልኝም አንተ የደም ሰው ነህ እዳለው “አባ” ሆይ “አባ” ሆይ! የዝንጀሮ መንገድ ቢከተሉት ገደል እስኪ ጭምርበት በበድል ላይ በደል “አባ” “አባ” ሆይ! የአክሱሙ እጨጌ እርስዎም የደም ሰው ኖት በእስጢፋን ቤ/ያን የፈሰሰው የንጽሑ ባህታዊ ደም ይፋረድቦታል እንደ አቤል ደም የባህታዊው ደም በጸባዖት ዛሬም ይጮኸል “አባ” ሆይ! “አባ” ሆይ! መፍትሔው አንድ ነው ሐወልትም አይደለም እሱም ንስሃ ነው።
- እንግዲህ “አባ” ሆይ! ጥይት የማይበሳው መኪና ገዝተዋል፣ መድፍ የማይበሳው ፓላስም በእምነ በረድ አሳንጸዋል፣ በሥምዎ ሐወልት ሰርተዋል የቀሮት ምርከብ ነው ወደብ ግን የሎትም!! ብዬ ስቀኝሎት በተሰበረ ልብ ነውና ቅኔዬ በተቀመጡበት ይቀበሉኝ።
- “አባ” ሆይ! ልጠይቆት እርስዎም ይጠየቁ ኸረ ለመሆኑ ገንዘቡ ከየት መጣ?
- “አባ” ሆይ! በሐውልትዎ የምርቃት ዕለት ስለ ሐወልቱ አሰራር መጽሐፍ ቅዱስ ይደግፈኛል ብለዋል አሉ። ልዑል እግዚአብሔር በህያው ቃሉ ላይ ደግሞ “በእውነት ላይ አትዋሹ” እንዲል “አባ” ሆይ ! የእርስዎ ውሸት ልዩ የሚያደርገው በፈጣሪና በሰው ላይ መዋሸዎ ነው። ምእመኑ መጽሐፍ ቅዱስ አያነብም ብለው ንቀውት ይሆን? ባይገርምዎት ምእመኑ ከእርስዎ ቀድሞ ሄደዋል። ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል እንዲሉ ያነሳዎት ጊዜ መልሶ ሲጥልዎት እንዳለፉት የኃይማኖት አንባገነን መሪዎች የበግ ለምድ ለብሰው ምዕመኑን ወደ ሲዖል እየነዱ እነሱም ሲዖል እንደወረዱ ሁሉ  ምስጢርዎ የሚገለጥበት ራቆትዎን የሚወጡበት እውነት የምትበቅልበት የሕዝብ እንባ የሚታበስነት እውነተኛ ዳኛ ልዑል እግዘአብሔር በጽድቅ የሚፈርድበት ጊዜው እሩቅ ነው ብለው ገምተው ከሆነ “አባ” ሆይ! መድኃኒአለም ወደልቦናው እንዲመልስዎት የናቁትና ያስለቀሱት ምእመን ሁሉ የዘወትር ጸሎት ነው።
- “አባ” ሆይ! በመፈንቅለ ካህን ስልጣን እንደያዙ አራስ የእጅዋን ትበለች እንዲሉ የእጅዎን የሚያገኙበት ወቅቱና ዘመኑ ቅርብ ነው ዕቃዎን ይጠቅልሉ!!
- “አባ” ሆይ! የአህያ ባል ከጅብ አያስጥልም እንዲሉ ምርኩዝ ያደረጉት የወያኔ ፖለቲካ እንደ ሸንበቆ ተሰብሮ ሳይወጋዎት አይቀርምና የምልግስሎት ምክር ቢኖር ንስሃ ገብተው የወያኔ የደመ-ነፍስ ፖለቲካ በቃኝ ብለው ወደ

*ፈጣሪዎ ጉያ ካልተሰብሰቡ እኔን ትቶ ሥጋ ለባሹን ክንዱ የሚያደርግ እርጉም ይሁን እንዲል ቅዱስ ቃሉ የታመኑባቸው የወያኔ ባለሥልጣናት ቀን የጨለመባቸው ዕለት ምድሪትዋን ለቀው ሲፈረጥጡ በዛ በክፉ ቀን ማምለጫው መሸሸጊያው መደበቅያው መድኃኒአለም ያልሆነለት ሰው "አባ" እርስዎ ብቻ ሆነው እንዳይገኙ እንቅልፍ የነሳኝ ጉዳይ ይሄ ነውና እባክዎትን ይመለሱ!!*

- *ሥም ከመቃብር በላይ ይውላል እንዲል ያገሬ ሰው "አባ" ሆይ! የወንጌል አርበኛ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይ ሥሙ ከተግባሩ ጋር አብሮ የሚሄደውን ለወንጌል ነፃነት ለኃይምማኖት የበላይነት እስከ የህይወት መስዋዕት ራሱ አሳልፎ የሰጠውን የብርሃናተ ዓለም የቅዱስ ጳውሎስ ሥም መምረጥዎ ዕንቁራሪት ዝሆንን አህላለሁ ብላ ውኃ ጠግባ እንደፈነዳች ሐዋሪያ ጳውሎስን እመስላለሁ ብለው እንደሆነ "አባ" ሆይ! ሥምዎና ተግባርዎ አራምባና ቆቦ ነው!! በመሰረቱ ሥም ሲወጣ ዳቦ ተቆርሶ ነው "አባ" ሆይ እርስዎ ግን እንደ ሀገሬ ቅኔ ዘራፊ የጳውሎስን ሥም ዝርፈው የቤተ-ክርስቲያኒትዋ ሀብትና ንብረት ዘርፈው በሥምዎ ሐወልት ያስቀረጹ የዘመናችን  የኃይማኖት ነጋዴ ሁሉ አማረሽ ገበያ አታውጥዋት እንዲሉ የወያኔ የደመ ነፍስ ፖለቲካ የሚያምሮት  ኃይማኖት የሚያቃዡት "አባ" ሥምዎ ከመቃብር በላይ ወይስ ከመቃብር በታች ይውል ይሆን?*
- *መካሪ የሌለው ንጉሥ ያለ አንድ ዓመት አይነግሥ እንዲሉ ለመሆኑ በዙሪያዎ የተኮለኮሉት ለኃይማኖታቸው ሳይሆን ለሆዳቸው ያደሩት በእውነት ሳይሆን በውሸት ያበጡት ኸረ ለመሆኑ በምእመኑ ላይ እርስዎ የሚያደርሱትን ግፍና በደል እንዲያቆሙ (እንዲተዉ) ወደ ፈጣሪዎ እንዲመለሱ ምክር ቢጤ አይለግስዎትም? ሐወልት ይቁሙሎት በማለት ከእግዚአብሔም ከሰውም ከሚያጥልዎት ይልቅ አቅሙ ካላቸው መልካምን ሥራ ይሰሩ ዘንድ አይረድዎትም? እንደው ለነገሩ ሃሳቡን አመነጨሁሎት እንጂ መልካም ነገርንም እንኳ የሚመክርዎት ቢኖሩ "አባ" ሆይ! የተገጠመሎት የዝሆን ጆሮ ስለ ሆነ ቸሩ መድኃኒአለም ልቦና ካልሰጥዎት ትዕቢት ውድቀትን ይቀድማል እንዲሉ የያዙት ስልጣን የተሸከሙት ሥም ያካበቱት ንብረት የዘረፉት ነዋየ ቅድሳት ልብዎ በትዕቢት ጢም ብላ እንድትሞላ ስላደረገዎት ሰማይና ምድር ያልፋል ቃሌ ግን ለዘልአለም ይኖራል ስለሚል ቅዱስ ቃሉ "አባ" ሆይ ወደ ህያው ህቃሉ ይመለሱ!*
- *"አባ" ሆይ! ዛሬ በዲሞክራሲና በኃይማኖት ሥም አባትና ልጅ የምድሪትዋ ሀብተ ነዋይ ተከፋፍላችሁ ሀገርና ወገን አራቁታችሁ ስታበቁ ይህን ደግሞ አልበቃ ብላችሁ እንደ ዛር የደም ነፍስ እያደናችሁ በወጣበት ስታስቀሩና እናት ወልዳ እንዳልወለደች፣ አጥብታ እንዳላጠባች፣ ለዓመታት ተሸክማ እንዳልተሸከመች፣ መልካምን ቀን በሩቅ እየተመለከተች የራስዋን ትታ የልጆችዋን ሆድ ሞልታ እጥፍ ብላ እንዳልተኛች ያለ ምንም ርህራሄ የወላድ መኃን ምድሪትዋም የወይታ ምድር ስታደርጉ፤ የንጹሐን ደም በከንቱ ሲፈስ ከዚህ ሁሉ ለማምለጥ ብርታት አግኝቶ መጠልያ ሰማያዊ ቤት አለች ብሎ ሸሽቱ ወደ ቤ/ያን ሲያደርግም እርስዎ ደግሞ ተቀብለው በማሳረፍ ፈንታ መስቀልዎ መርዛማ እሾህ ሆኖ የዜጎችን ልብ ሲያደማ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ ኳስ ስትቀባበሉት* **ኤልሮኢ!!!** *እግዚአብሔር አይተዋልና ምሕረትን እንዲለምኑ ነው የምማጸኖት።*
- *"አባ" ሆይ! እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ ጠባቂው በከንቱ ይደክማል እንዲል ቅዱስ ቃሉ የተመኩበት ምእመኑን የናቁበት ኃይማኖታችንን ያዋረዱበት ምስጢሩ ምን ይሆን? በጠባቂዎችዎ ነው ወይስ እርቃኑ በቀረው በወያኔ ፖለቲካ? ኸረ ለመሆኑ ምስጢሩ ምንድ ነው? ንጉሥ ሰሎሞን ሁሉ ከንቱ የከንቱ ከንቱ ነው እንዳለው ሐወልት አቁሜለሁ ሲሉ መለከት እንደነፉ ሁሉ አሁንም ምንም ሱሪን በአንገት እንደማለት ከባድ ቢመስሎትም ወደ ብርሃናት አምላክ ወደ ቸሩ መድኃኒአለም በንስሃ ተመለሰው የበደሉትን ሕዝብ ይቅርታ ይጠይቁ!*
- *"አባ" ሆይ ይህንን አምላካዊ  ቃልና ምክር የተምላበትን ጽሑፍ አንብበው አስተውለ ቆም ብለው ምንጋ እንደ ቆሙ ራስዎን አይተው በሚወስዱት እርምጃ የወደፊት ዕድል ፋንታዎ ወይም ዕጣዎ ወይ የዘለለም ሕይወት አለያም ደግሞ የዘለልም ጥፋት ይጠብቆታልና "አባ" ሆይ! ሳይሞሽቦት አሁኑ ህይወትን ይምረጡ!!!*
- *"አባ" ሆይ! እንደ ያዛ ያልተፈቀደሎት እንደ አካን የተከለከለውን እንደ ይሁዳ ደግሞ ክብርንና ባለጠግነትን አንገብግቦት በማን አለብኝነት መንፈስ እጆትን መስደድዎንና በክብሬ እቀናለሁ ያለ እግዚአብሔር ብቻውን በሚመልክበት ሥፍራ ለመስተካከል ሐወልት ማቆሞትን ቀጣይ ትውልድን አስበውና የንፁሐንን ልብ ለመመረዝ ሆን ብለው ይህን ሐወልት በምስልዎትና በሥምዎት በማቆምዎ ተመዝነው እጅግ ከመቅሎልዎት በላይ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ለማድረግ ራስዎትን ሸጠዋልና ዋይ! ይበሉ።*

***ዲ/ን ሙሉጌታ ወልደገብርኤል***